## ዋለልኝ መኮንን ና የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ

በቅርቡ በየዓመቱ የሚከበረው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓልና አምስተኛው ዓለም አቀፍ የፌዴሬሽን ጉባዔ በአገራችን ሲስተናገድ ሰንብቷል። የብሔር ብሔረሰቦች ቀን እንደ በዓል መከበሩ አስፈላጊነት በኤትኒክ መርህ ላይ የተመሰርተውን የፌዴራል ስርዓት አጽናዖት ለመስጠት የታሰበ መሆኑ ቢታወቅም ግን ዋናውና አሌ የማይባል አዲስ ተዋጾዖው ማንነታቸው ተረስቶ ና ተንቆ በገዛ አገራቸው የሁለተኛ ደረጃ ዜግነት የነበራቸው ህዝቦች አዎን አለን ፤ ነበርን ፤ እንኖራለንም ብለው ራሳቸውን በአደባባይ የሚገልጹበት፤ ባህላዊ እሴቶቻቸውን የሚያሰተዋውቁበት በጋራ የፌስቲቫል ስሜት አንድነታቸውን ተስፋቸውንና የአገራቸውን ሰላም የሚዘክሩበት ቀን መሆኑ ነው።

በዚሁ ወቅት ለአምስተኛ ጊዜ የተካሄደውን ዓለም አቀፍ የፌዴሬሽን ጉባዔ አገራችን ዕድሉን አግኝታ በአፍሪካ የመጀመሪያው አስተናጋጅ አገር ለመሆን መብቃቷ ና ከዚሁም ጋር አገራችንና በውስጧም የሚኖሩትን ህዝቦች ለዓለም ህብረተሰብ ለማሰተዋውቅ ትልቅ መድረክ  የፈጠረ መሆኑ ትኩረት የሳበ ጉዳይም ሆኖ ነበር።

ሆኖም ግን የጉባዔው  በኢትዮጵያ መካሄድ በአገሪቱ የሰፈነው የፌዴራላዊ ስርአትና መንግስታዊ አወቃቀር ፍጹም ተወዳሽ ና እንከን የለሽ ያደርገዋል  ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም  በውስጡ ችግሮች ያሉበት ወደፊትም ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ያረገዘ  ነው። ማንኛውም ፌደራሊዝም ፍጹምና እንከን የለሽ ሊሆን ካለመቻሉ ጋር በይዘቱም በቅርጹም እንደ አካባቢውና አገራዊ ተጨባጭ ሁኔታ ብዙና ተለዋዋጭ መልኮች ያሉት በመሆኑ የኢትዮጵያም ፌደራሊዝምም በዓለም ላይ ከተከሰቱት ከብዙ የፌዴራሊዝም ቀለማት መካከል እንደ አንዱ  ሆኖ መጠቀስ የሚችል ብቻ ነው። ዓለም አቀፍ የፌዴሬሽን ጉባዔ የተወጠነበትና በየአመቱ በተለያዩ የዓለም ክፍላተ ሃገራት የመማማርና የልምድ ልውውጥ ጉባዔውን የሚካያሂድበት ምክንያትም ፌዴራሊዝም በጊዜና በቦታ ያለውን የመለዋወጥ ባህርይና እድገት ግንዛቤን መሰረት በማድረግ ነው።

የዛሬው ኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ጥንስሱ የተቋጠረውና የንድፈ-ሃሳብ ቀመሩ የተቋጨው ገና በሰባዎቹ የተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ሲሆን ፋና ወጊ በመሆን ቁልፍ ሚና የተጫወተውም ዋለልኝ መኮንን ነው። ዋለልኝ መኮንን የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ  ፌዴራሊዝም የነፍስ አባት ነው ቢባል  ማጋነንም አይሆንም።

በኢትዮጵያ ማርክሲዝምን በማስፋፋቱም ሆነ በመተገበሩ የተካኑ እንደ ኃይሌ ፊዳና የመሳሰሉ የማርክሲዝም ሊቃነ-ጳጳሳት ቢኖሩም ዋለልኝ መኮንን ግን የማርክሲዝምን ጠበል ከኢትዮጵያ አፈር ጋር አጎዱ ብሎ ያዋሃደ የመጭውንም ዘመን ብስራትና መርዶ የነቀሰ ኢትዮጵያዊው የማርክሲዝም መጥምቁ ዮሃንስ ነበር።

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ያለ ኮምኒስት ማንፌስቶ እንደማይታሰብ ሁሉ ማርክሲዝምም በኢትዮጵያ ያለ ዋለልኝ ማንፌስቶ ኢትዮጵያዊ ደምና ስጋ አይኖርውም። የዋለልኝ ማንፌስቶም በ1961 እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ያቀረበው ጽሁፍ ነበር። ይህ የዋለልኝ ጦማር የ "የዛ ትውልድ" መንፈስና ንቃተ ህሊና የተቋጨበት ትውፊት ነበር። ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ  ባለፈው ነሃሴ ወር ኦነግ ላዘጋጀው ፎረም ባቀረበው

**ጽሁፍ ይህ የዋለልኝ ማንፌስቶ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ላይ የነበረውን ሚና ሲገልጽ እንዲህ ሲል አወስቶታል የጽሁፉንም ዋና ዋና ነጥቦች እንደሚከተለው አሳጥሮ አቅርቦታል።**

"Walleligne's paper is probably the most influential short paper that shaped both the views of the radical "internationalist" left and the ethno-nationalist movements in Ethiopia.
Walleligne's paper can be summarized in some seven interrelated propositions.

- That Ethiopia is not one nation but a country made of a "dozen" nationalities. Each with its own
  language and cultural identity
- Ethiopian Nationalism is "fake" and advanced by the ruling class and "unwillingly accepted and even propagated by innocent fellow travelers." Furthermore, this "fake" nationalism is nothing but the supremacy of Amhara-Tigre. This is attested by the symbols of Ethiopian Nationalism such as Amharic music, Orthodox Christianity, the Amhara-Tigre Shamma, and the like
- The cultural and economic oppression of nationalities by the Amharas and their junior partners, the Tigres is not because Amharas and Tigres have inherent imperialist tendencies. Rather it is a historical accident. If the others (for example the Oromos or the Wolaytas) get a chance, they would have done it and they have tried to do so.
- Ethno-nationalist movements by themselves could not deliver the equality we seek, because these movements are exclusive in character and generally led by the bourgeoisie and/or feudal lords. So, we don't expect ultimate deliverance from them.
- Still, we should support these nationalist movements because they weaken the state and thus prepare the ground for a socialist revolution, even if they are secessionists.
- Secession is OK as long as it is led by socialists (workers and peasants) and "believes in its internationalist obligations." This is especially true if the rest of society is not ready for a socialist revolution.
- The key issue is the commitment of the movement to socialist ideology, not national integrity. Because "in the long run, socialism is internationalism and a socialist movement will never remain secessionist for good." That is why, North Korea's secession from the South, for example, is supported by the left."

**የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ የኤትኒክ ፌዴራሊዝም ሲታሰብና ሲቀመር ይህንን የዋለልኝን ረቅቅ የንድፈ-ሃሳብ መሰረት ተንተርሶ እንደነበር ግልጽ ነው። የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ቀራጮች ደደቢት በረሃ ሳይገቡ በፊትና ጠብመንጃና ጥይት ከመታጠቃቸው በፊት የታጠቁትና የተቀረጹት በዋለልኝ መንፈስ ነበር።**

ዋለልኝ መኮንን እንደ ግርማሜ ና መንግስቱ ንዋይ በ medieval ዓለም ውስጥ የነበረውን ጨቋኝ ፊውዳል ስርአት ላይ ያመፀ ህይወቱንም ነፍሱንም ለትግሉ አሳልፎ የሰጠ ብርቅና ድንቅ ከሚባሉት የተማሪዎች ንቅናቄ ኮከብ መሪዎችና ተዋንያን መካከል አንዱ ነው። ዋለልኝ የትውልዱ ቋሚ መለዮ የሆኑት ባህርያት ማለትም ፤-ስር-ነቀልነት፤ ወግ-ዘርጣጭነት (iconoclastic)፤ ማርክሲስትነትና መስዋዕትነት ሙሉ መገለጫ ተምሳሌ ነው።

ግን የዋለልኝ መኮንን ሚና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ያሳረፈው ተጽዕኖ የኤትኒክ ፌዴራሊዝምን ከመቅረጽ በላይ የዘለቀ ነው። ዋለልኝ የትውልዱን የፖለቲካ ባህልና መንፈስ የጫረ የትግሉንም ሂደት ፈር የቀደደ በኢትዮጵያ ከጥቂት የግራ ፖለቲካ "Founding Father" ተብለው ከሚጠቀሱት አንዱ ሆኖ የሚታወስ ነው። ዋለልኝ የ"የዛ ትውልድ" ሁለነተናዊ ማንነት ወካይ ገጸ-ባህርይ የፖለቲካውም አካላዊ መገለጫ (personification) ነው።

"All politics are local" ይባላል። የፖለቲካ መስመሮች ግራ ቀኝ ተበለው በርዕዮት ተከፍለው በጋራ ቅጽል ስም ይጠሩ እንጂ ፖለቲካ በየአገራቱና በየአካባቢው ራሱን የቻለ ባህርይና የራሱ ማንነት አለው። ማርክሲዝምና በአጠቃላይ የግራ ፖለቲካም በኢትዮጵያ የራሱ አገራዊ ማንነት፤ የራሱ ኢትዮጵያዊ መልክና የራሱ ሰውነት አለው። የራሱም ስም አለው። ሱሙም ዋለልኝ ይሆናል። ወይም በአንብቢ ፈቃድ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ዋለልኝዝም ይለዋል። የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ዋለልኝዝም የሚለውን ቃል በዚህ መጣጥፍ ውስጥ የሚጠቀምበት መላው የኢትዮጵያ ማርክሲስትና ግራ ዘመም የፖለቲካ መስመሮችን በጥቅሉ ለመጥራትና ከዚሁም ጋር ተያይዞ ለአመታት የተካበተውን የፖለቲካ ባህልና የስነ-ልቡና ስሪት በአንድ ማሰሪያ ቃል ለመግለጽ ሲሆን በዋለልኝ መጠራቱ ደግሞ የዚህ ሁሉ የመጀመሪያው ጠቋሚ ኮከብ በመሆኑ ነው።

የዋለልኝ መንፈስ ባለፉት አርባ አመታት የኢትዮጵያን የፖለቲካ መድረክ የተቆጣጠረና ለሚቀጥሉትም አስርተ አመታት ጥላውን እንዳጠላ የሚቆይ መንፈስ ነው። ዋለልኝዚም የ "የዛ ትውልድ" የአስተሳሰብ ስልት፤ የአመለካከቱ ማቀፊያ (framework)፤ የሁለንተናዊ ማንነቱ መገለጫ ባህሉ ነው። ዋለልኚዝም የኢህአፓን የመሳሰሉት የኦነግና የመሳሰሉት ዳዊት ነው። ዋለልኚዝም የኢህአደግ አብዮታዊ ዲሞክራሲ መሰረት ነው። ዋለልኚዝም የኢትዮጵያ pseudo liberals ተቃዋሚዎች እውነተኛ ማንነት ነው። ዋለልኝዝም የሁሉም የፖለቲካ መስመሮች እርሾ ወይም ጥንስስ matrix ነው። ያለ ዋለልኝ መኮንን ኢህአፓን ወይም ኢሰፓን ማሰብ አይቻልም። ያለ ዋለልኝ መኮንን ከኢህአደግ እስከ ኦነግ ከመድረክ እስከ ግንቦት ሰባት ያሉትን ድርጅቶች ማሰብና ማወቅ አይቻልም። ዋለልኝ በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ አልነበረም ወይም ራሱ አልፈጠረም ግን ዋለልኝዝም በነሱ ውስጥ አለ። የሱ እርቃነ መንፈስ (ghost) ናቸው።

በኢትዮጵያ ካለፉት ሰላሳና አርባ አመታት አንስቶ ሁሉም ዜጎች የሚመኩበትና የሚኮሩበት፤ ቢያንስ ሁሉም ተዋንያን በእኩል የሚሳተፉበት ቢያንስ ከሞላ ጎደል የሆነ ስርአት ለመፍጠር መንገዱ የረዘመበት ዋንኛው ምክንያት በዋለልኝዝም ባህል ምክንያት ነው። ኢህአደግ በምንም ተአምር ከአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ በስተቀር ሌላ ምርጫ እንዳይኖረው ያደረገውና የሚያደረገው የተፈጠረበት አስኳል DNA

ዋለልኝዝም  በመሆኑ ነው። የተቃዋሚ ድርጅቶች ርስ በርስ የሚቆራቆዙበት ምክንያትና አልፎም ማናቸውም ቢሆኑ ለስልጣን ቢበቁ ከኢህደግ ርቀው የተሻሉ የማይሆኑበት ምክንያት የተጸንሱበት ማህጸን የዋለልኝዝም ባህል ውስጥ ስለሆነ ነው። አነግን ሰላሳ አመት ዱር ለዱር የሚያዞረው፤ ግንቦት ሰባትን ለፋኖ ተሰማራ ያበቃው የዋለልኝ መንፈስ ነው።  ቅንጅትን ፈጥሮ ያፈረሰና መድረክን የተካ የዋለልኝዝም አስማትና ጥበብ ነው።

የ wikileaks በኢትዮጵያ ላይ ያወጣው ምስጢርም በቀጥታም ባይሆን ይህንን እውነታ በተዘዋዋሪ የሚመሰክር ነው። wikileaks በኢትዮጵያ ላይ የነበረው ምስጢራዊ መረጃ ብዙዎቹ እንደሚያስቡት ጠ/ሚንስትሩ ለ "vegetation" ያላቸውን ዝንባሌ በግልጽ መናገራቸው ብቻ አይደለም።  ዋናውና ትልቁ ምስጢር ጠ/ሚንስትሩ በቃላት መሃከል ለአሜሪካኖቹ ያስተላለፉት መልዕክት ነው።

ጠ/ሚንስትሩ ለአሜሪካኖቹ ያሉት ...አዎ እኛ የምናካሂደው ከናንተ የተለየ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ነው ...በዚህም ብትቃወሙን ይገባናል .. ተቃውሚችሁንም በጸጋ እንቀበለዋለን .. ግን እኛን መቃወም የኛን ተቃዋሚዎች ደጋፊ ሊያደርጋችሁ አይችልም .. ምክንያቱም እነሱም ከኛ የተሻሉ አይሆኑም .. እኛም እነሱም ለዲሞክራሲ አንበቃም ግን እኛ እንሻላችኋለን ነበረ መልዕክታቸው። "meles said his country's inability to develop a strong democracy was not due to insufficient understanding of democratic principles, but rather because Ethiopians had not internalized those principles".

ጠ/ሚንስትሩ ይህን ሲናገሩ ለማለት የፈለጉት  ቋሚና ዘላቂ ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ዛሬውኑ ለማቆም ማህበራዊ መሰርቱ የለም መካከለኛ ገቢ ያለው መደብ አልተፈጠረም። የኢትዮጵያ ህዝብ በአብዛኛው ያልተማረ አርሶ አደር ነው የዲሞክራሲ "stake holder" አይደለም ማለታቸው ብቻ አልነበረም።

በዚህ የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ማንኛውም የፖለቲካ ደርጅት ዲሞክራሲን በፍላጎት ብቻ እንደ ስጦታ ማበርከት አቅሙ አይኖረውም። የተቃዋሚዎችም የዲሞክራሲ ዲስኩር ከዲስኩርነት አያልፍም ማለታቸውም ብቻ አይደለም።

በሌላ አነጋገር ጠ/ሚንስትሩ ለማለት የፈለጉት አገሪቱ ለሙሉ ዲምክራሲያዊ ግብረ-ሰናይ ያልተዘጋጀችውን ያህል በዛው መጠን ልክ እኛም የመንግስትም ሆነ የተቃዋሚው ፖልቲከኞቹ ለዲሞክራሲያዊ ምግባረ-ሰናይ አልበሰልንም አልደረስንም ማለታቸው ነበር።

ስለ ዲሞክራሲ እውቀት ምጥቀቱ ቢኖረንም እኛም የአገራችንና የህዝባችን አካል እንደመሆናችን ከጠቅላላው የቀድሞ ባህላችንና ልምዳችን ጎታች ሃይል (inertia) አልተገላገልንም ማለታቸው ነበር።

አሜሪካኖቹም ይህንን ድሮውንም ያብሰለሰሉትት ጉዳይ ነበርና ..ከሚያውቁት Don kihot ያው የለመዱት Macho ይሻላል ..ብለው ጣራ ጣራውን እያዩ "ተቃውሚቸውን" አሰምተው ነበር የተለያዩት።

ጠ/ሚንስትሩን ግን በግልጽነታቸው አድናቆት ሊቸራቸው ይገባል። ቢያንስ ከእኛ ዲሞክራሲ ወዲያ ላሳር ብለው ራሳቸውንም ሌላውንም ለመሸንገል አልዳዱም። ቢያንስ ራሳቸውም የችግሩ ሰለባና አካል መሆናቸውን በማመን የትውልዱን ድክመት በግልጽ አስቀምጠዋል። በመሰላቸው መንገድም ሊፈቱት እየሞከሩ ነው።

ጠ/ሚንስትሩ ፖልቲከኞቹን አስመልክቶ "Ethiopians had not internalized those (democratic) principles" ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ስለ ዲሞክራሲ እውቀት ምጥቀቱ እያላቸው ራሳቸውን ከዲሞክራሲ ጋር እንዳያስማሙ መንፈሳቸውን ገንዞ የያዘው አስማት እሱ ምንድነው? ጥረታቸውን የሚያኮላሸውስ ድግምት ምን ይሉታል? ትልቁ የአገራችን ፖለቲካ እንቆቅልሽ ያለው እዚህ ላይ ነው።

ጉዳዩ እንቆቅልሽ መስሎ ይታይ እንጂ ግን እንቆቅልሽ አይሆንም። ኢትዮጵያውያን የተፈጠርንበትና የተቀረጽንበት ስርአት የፊውዳሉና የአብዮታዊው ስርአት እንደመሆኑ የጥያቄው መልስ ተፈልጎ የሚገኘው በዚሁ ውስጥ ይሆናል። የፊውዳሉም ሆነ የአብዮታዊው ስርአት መንፈሳዊና ባህላዊ እሴቶች ከዲሞክራሲያዊ ስርአት እሴቶች ጋር የማይጣጣሙ ብቻ ሳይሆን የሚጋጩ እንደመሆናቸው እኛም ጥርስ ነቅለን ያደግንበትና የኖርንበት በእነኝህ እሴቶች ውስጥ እስከሆነ ድረስ ምንያህል ስለ ዲሞክራሲ ብንራቀቅ ውስጣችንን ለመለወጥ አስቸጋሪና ፈታኝ በመሆኑ ምክንያት ነው።

የፊውዳሉ ስራት እሴቶች የአንድ ዘር የበላይነት የሚያጸድቅ፤ ስልጣን ደምና አጥንት እየተቆጠረ የሚወረስበት፤ መሬትና ሃብት ለባላባቱ መደብ የታደለበት፤ ዘረኝነት፤ ትምክህተኝነት፤ድንቁርና፤ አድልዎ፤ጉቦ፤ብዝበዛ...ወዘተ ተቀባይነት (vertue) ያደረገ ነበር። የፊውዳሉ ስራት ካለፈ ግማሽ ምዕተ አመት ያለፈው ቢሆንም መንፈሳዊና ባህላዊ እሴቶቹ ግን አሁንም ህያው ናቸው። ይህ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካውም ውስጥ ይንጸባረቃል። በቅንጅት አባላት ውስጥ ዶ/ር ብርሃኑ በወቅቱ የታዘበው ለዚህ ጥሩ መግለጫ ነው። " ...Some could even be down-right chauvinists covering their deeper identity based positions under the ambit of liberalism or national integrity". ሲል ታዝቧል።

ሌላው ደግሞ ሞገደኛው አብዮታዊ ጊዜና ያሳለፍነው አብዮታዊው ስርአትም በእያንዳንዱ ዜጋ የአስተሳሰብና የስነ-ልቡና መሰረቶች ላይ የራሱን ማህተም አትሞ አልፏል። ይህን ማህተም ነው የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በአንባቢ ፈቃድ በአንድ ቃል ዋለልኝዝም እያለ የሚጠራው።

የዋለልኝዝምን ቅርስ አንድ ሁለት ብሎ ከመቁጠሩ በፊት ለመንደርደሪያ ለአፍታ ወደኋላ መለስ ብለን ትንሽ እንቃኝ።

ከምኒሊክ ጊዜ አንስቶ እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ የነበሩ የኢትዮጵያ ምሁራን የአገሪቱ የማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የእድገትና የለውጥ እርምጃ ከተራማጁ ንጉስ ጋር በማበር ይፋጠናል የሚል የጥገናዊ ለውጥ መስመር የሚከተሉ ነበሩ። ትግላቸውም ለሁለገብ እድገት እንቅፋት በነበሩትና በህዝቡ ላይ አስከፊ የጭቆናና የምዝብራ ቀንበራቸውን በጫኑት የየአካባቢው የፊውዳሉ ስርአት ኢሊቶች ላይ የተነጣጠረ ነበረ። ሆኖም ግን አላማቸው፤ እምነታቸውና ልፋታቸው ከሽፎ መቅረቱ ግድ ነበርና ከዚያ የለጠቀው አዲስ ትውልድ የቀድሞው ትውልድ ትግል ስኬት ማጣት በመመልከትና የስርአቱ

ፍጹም ጸረ-ለውጥ ተፈጥሮ ለፐገናዊ ለውጥ ቦታ እንደሌለው በማጤን የትግሉን ግብና አላማ ስር-ነቀል የስርአት ለውጥ እንዲሆን ያደርጋል።

የ1953ቱ የነግርማሜ ና መንግስቱ ንዋይ መፈንቅለ-መንግስት ሙከራ የዚህ የትግል አቅጣጫ የመጀመሪያው አብሳሪ ደወል ሲሆን የተማሪዎች ንቅናቄም ይህን ፈለግ መከተል ይጀምራል። ጥላሁን ግዛው የአ.አ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፕሬዝዳንት ስለ ስርአት ለውጥ በተናገረ በጥቂት ቀናት ውስጥ በነጭ ለባሾች አ.አ መንገድ ላይ በጥይት ተደብድቦ እነደነ ግርማሜ ንዋይ ህይወቱን መክፈሉም የዚሁ ሂደት አካል ነበር። በፊውዳሉ ስርአት የመጨረሻ አመታት የአገሪቱ የፖለቲካ ትኩሳትና ንዝረት እያየለ የተማሪዎች አመጽ ይህንኑ በማንጸባረቅ እንደ ሰደደ እሳት እየጋመ ከመመጣቱ ጋር ስር ነቀል ለውጥ ከመሻት ባሻገር የትግሉ ቀጣይ መድረሻውን በተማረው ዘንድ በውል የሚያውቅና የሚታወቅ ነገር አልነበረም። በዚሁ ወቅት ነበር በሳይንሳዊነቱ በጥብቅ የሚታመነበትና ለሁሉም የህብረተሰብ ጥያቄዎች መልስ የነበረው ማርክሲዝም ሌኒንዝምም በአለም ገኖ ንቅናቄውም ሰፍቶ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የደረሰው። ለውጥ ለተጠማውና ግን ለውጡ እንዴትና ምን ሊሆን እንደሚችል በቂ ስዕል ላልነበረው ለነ ዋለልኝ ትውልድ ማርክሲዝም ከሰማይ የወረደ መና ያህል የሚታይ ዋጋ ነበረው። የማርክሲዝም የአብዮታዊ ለውጥ ጥሪ ከስር-ነቀል የለውጥ ፍላጎት ጋር የሚጣጣም ብቻ ሳይሆን ለትግሉ ንድፍ-ሃሳባዊ መሰረት የሰጠና መንገዱንም የሚያሳይ ነበርና በሆታና በእርካታ ተቀባይነት ማግኘቱ ግድ ነበር።

እዚህ ላይ ሳይጠቀስና ሳይሰመርበት የማይታለፍ ቁም ነገር ቢኖር በወቅቱ "ያ ትውልድ" በማርክሲስት ጎዳና መሰለፉ የማይታጠፍ ታሪካዊ ሂደት የሚያደርገው የዛ ግዜ ነባራዊ ሁኔታ እንደመሆኑ ከዛሬ የግዜ ተራራ ላይ ቆሞ ያለፈውን ግዜ ቁልቁል እያዩ ታሪክን ማቅናት እንደማይቻል ሁሉ መኮነን ደግሞ ታሪክን አለመገንዘብ ብቻ ሳይሆን "ያ ትውልድ" የፊውዳሊዝምን ቀንበር ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለመጣልና የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነት ለማረጋገጥ፤ በመሰለውም መንገድ ፍትሃዊ ስርአት በአገሪቱ ለማስፈን የከፈለውን የትግል መስዋዕትነት መካድ ይሆናል።

በመሆኑም ነው የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ለዋለልኝ መኮንንና ለሌሎቹም የኢትዮጵያ ግራ ፖለቲካ አባት መስራቾች ያለው ከፍ ያለ ክብርና አድናቆት እንደተጠበቀ ሆኖ እነሱ ከቆሙበት ቦታ በመነሳት አሁን እንዴት ወደፊት መቀጠል ይቻላል የሚለውን ጥያቄ በሃሳብ መልክ የሚያነሳው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ እድገትና እርምጃ እነሱ ጥለውት ካለፉበት ብዙም ርቆ እንዳልሄደ የሚታዩት ተድጋጋሚ ክስተቶች የሚያረጋግጡት እውነታ ነው። ዋለልኝዝም እንደ የግራ ክንፍ ፖለቲካ የአስተሳሰብ ቀመርና ዝንባሌ በነዋለልኝ ግዜ በትውልዱ ተቀባይነት ቢኖረውና ትክክለኛ መንገድ ነው ተብሎ ቢታመንበት ወቅቱ ነውና ተገቢ ይሆናል ። በአሁኑ ዘመን ግን ዋለልኝዝም የአስተሳሰብ ኋላቀርነትና ብቻ ሳይሆን እንደምንርዳው ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አንዱ እንቅፋትና በሽታ ፈጣሪ መሆኑ ነው። ዋለልኝዝም (Ethio-mutant marxism) ማለት ነው።

ማርክሲዝም ሌኒንዝም ኢትዮጵያ ከደረሰና ኢትዮጵያዊ ደምና ስጋ ለብሶ ወደ ዋለልኝዝም ከተቀየረ በኋላ ያለው ታሪኩ ሁሉም የሚያውቀው ታሪክ ነው። ይህም ከ1966 እስከ አሁን ያለው የኢትዮጵያ ጉዞና ጎዳና ነው። በየካቲት አብዮት አድርጎ፤ሶሻሊስት ኢትዮጵያን ቆርቁሮ፤ በቀይና የነጭ ሽብር የደም ጎዳና ተጉዞ፤ የሰሜን ተራራና በረሃን አደበላልቆ፤ ሌላ የግንቦት አብዮት ሾሞ፤ ሁለት አገር መስርቶ፤ ፌዴራል ኢትዮጵያን አዋቅሮ አሁን ድረስ ቀጥሏል። ቅርጹን እንጂ ይዘቱን ሳይቀይር ወደፊትም ይቀጥላል።

ከዋለልኝዝም የወረስነው ባህል ዋናዎቹ :- አንደኛ) ከፖለቲካ ተፎካካሪነት ይልቅ የፖለቲካ ጠላትነትን።

በማርክሲዝም የመደቦች ቅራኔና ትግል የህብረተሰብ እድገት ሞተር እንደሆነና የሚፈታውም አንዱ ሌላውን በማጥፋት ወይም አንዱ በሌላው በመዋጥ መሆኑ የሚያወሳው ሃሳባዊ ቀመሩ የርዕዮተ-ዓለሙ ቁልፍና ምሶሶ ነው። ከዚህ በመነሳት ዋለልኝዝም ማናቸውንም የፖለቲካ ሂደትና መስተጋብር የሚመለከተው በመደቦች ትግል መነጽር ነው። እንደ መደብ ትግሉ ሁሉ ፖለቲካውም ቅራኔ ተኮር ከመሆኑ ጋር  የፖለቲካ ጠላት እንጂ የፖለቲካ ተፎካካሪ አያውቅም።  የፖለቲካ አቻ አይቀበልም። ይህ የአስተሳሰብ ቀመር የፖለቲካ ልዩነትን በአንድነት ውስጥ ማስተናገድ አይችልም። በዚህ የአመለካከት መነጽር ማየት የሚቻለው የፖለቲካ ጠላትነትን ብቻ ነው። በዚህም ምክንያት በዋለልኝዝም መስጠትና መቀበል (win win) የሚባል መውጫ መንገድ ማየት አይቻልም። በዚህ የአስተሳሰብ ማዕቀፍ ማሸነፍ ወይም መሸነፍ እንጂ እየተቃረኑ አብሮ መስራት አይታወቁም። ከተፈጥሯዊ ባህርዩ ጋር አይግጥሙም።

*-በዚህም ምክንያት ቀደም ሲል የርዕዮተ-ዓለም ጥራት ልዩነት በሚል ብቻ አንድ አመለካከት ያላቸው ቡድኖች ርስ በርስ የተፋሰሱትን ደም ታሪክ በሰቀቀን የሚያስታውሰው ነው።*
*-ዛሬም በየግዜው ብቅ የሚሉት ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚመሰረቱት ህብረት  የጠላቴ ጠላት በሚለው መርህ የሚሆንበት ምክንያትም መሰረቱ ይኸው ነው። ህብረቱም ግፋ ቢል ጠላት የተባለው እስከሚጠፋ ድረስ የሚዘልቅ አሊያም ከወዲሁ የሚናድበት ምክንያትም ይኸው የአስተሳሰብ ውርስ ውስጥ ለውስጥ (sub-consciously) ስለሚሰራ ነው።*
*-ኢህአደግም ተቃዋሚዎቹን በ"ጠላትነት" የሚፈርጀውና ለአመጽና ለጦርነት የሚገፋው በዚሁ ምክንያት ነው።*
*-ይህን  የኢህአደግ ግፊያ ምክንያት አድርገው ለአመጽና ለጦርነትም የሚነሱ የሱን የ"ጠላትነት" ስነ-ልቡናውን ስለሚጋሩት ነው።*

ከዋለልኝዝም የወረስነው ባህል:- ሁለተኛ) የፖለቲካ "ጠላት"ን ማጥፋት ወይም መደምሰስ።

የመደብ ትግል የሚፈታው በአብዮት፤ የመደብ ጠላትን በማጥፋት ነው። ይህ የማርክሲዝም የአብዮት ንድፈ-ሃሳብ ነው። በሃይልና በአመጽ መንገድ ስር ነቀል ለውጥ አራማጅነት ከማርክሲዝም መምጣት በፊት የነበረና ለአገራችን ለተማረው ክፍል እንግዳ ሃሳብ ባይሆንም ከማርክሲዝም መምጣት ጋር የሃይልና የአመጽ መንገድ በአብዮታዊ ለውጥ ንድፈ-ሃሳብ መሰረት ማግኘቱ ለአሰቃቂና አሳዛኝ የታሪክ ምዕራፍ አብቅቷል ። አብዮታዊ ለውጥ በማርክሲዝምና በኋላም በዋለልኝዝም ልዩ ትርጉም ያለውና ራሱን የቻለ ባህል ነው። አብዮታዊ ለውጥ ማለት የፖለቲካ ጠላትን በአካል መደምሰስና ማጥፋትን ማለት ነው። አብዮታዊ ለውጥ ራስን በፈቃደኝነት መሰዋዕት ማድረግ ማለት ነው። የፖለቲካ ጠላትን ማጥፋትና ለዚህም ህይወትን አሳልፎ መስጠትን ቅዱስ ባህል ያደርጋል። በዚህም ባህል መሰረት መሞትና መግደል የአብዮተኛነት የሞራል መለኪያ መስፍርቶች ይሆናሉ። የሰው ነፍስና  የደም ግብር የአብዮት ህልውና መሰረት ነው። "አብዮት ልጆቿን ትባላለች" የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው። ዋለልኝዝምም መሞትና መግደል እንደ ልዩ ቅዱስ ስራ እንዲቆጠሩ ያደርጋል።

*-የደርግን፤ የአሲምባን፤ የደደቢትን የኦነግን ወዘተ መዝሙሮች የሰማ ሞት መፍራት ነፍስ አለማጥፋት አይቻለወም።  የማርክሲዝም የአብዮት አንድምታ የህይወትን ውድነት ያረክሳል። ለሰው ነፍስ ዋጋ አይሰጥም። የግለሰብን ህይወት ፋይዳ ቢስ ያደርጋል።  በዚህም ምክንያት እንደ*

*ማርክሲዝም ዋለልኝዝም ሰው በላ ሽብሮችን፤ ጦርነቶችንና ስታሊኖችን መፍጠሩ የማይቀር ግዴታ ነበር። ወደፊትም ይፈጥራል።*

ከዋለልኝዝም የወረስነው ባህል፡- ሶስተኛ) የስልጣን አምልኮና አምባ-ገነንነት

ይህ ባህርይ ከማርክሲዝም የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ የሚመነጭ ነው። በዋለልኝዝም የሁሉም ነገር ተዋረድ ከታች ወደላይና ከላይ ወደ ታች ነው። የአግድሞሽ ግንኙነት ወይም በእኩልንትና በአቻነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት አይኖርም። ይህም መርህ የስልጣንን ፍጹምነትና በማጽደቅ የተክለ-ሰውነት አምልኮን (personality cult) ኮትኩቶ ያሳድጋል።

*-ዋለልኝዝም ሁሉኑም እሽሩሩ ከሚለው ከዲሞክራሲያዊ አሰራር ጋር የማይታረቅ ቅራኔ የሚኖረው በዚህ ምክንያት ነው። በዝህ መርህ መሰረት በአንድ ድርጅት ውስጥ ወይም በአንድ አገር ውስጥ ምንግዜም አንድ ብቸኛና ትክክለኛ ሃሳብ አለ። አንድ ብቸኛና ሁሉን አዋቂ መሪ አለ፤ አንድ ብቸኛ አውራ መሪ ድርጅት አለ። ሁሉም ግኑኝነት ከላይ ወደ ታች ከታች ወደ ላይ የገዥና የተገዥ የአዛዥና ታዛዥ መርህ ላይ የተመሰረተ ይሆናል። በዚህም ምክንያት የስልጣን ፉክክር የሞት ሽረት ትግል መልክ ይይዛል። ስልጣን በድርጅት ደረጃ የግል ወንበር ይሆናል። በአገርም ስልጣን ማገልገያ ቤት (public office) ሳይሆን ዙፋናዊ አንድምታ ይኖረዋል።*

ጠ/ሚንስትሩ በአገራችን ዲሞክራሲያዊ ስርአት ለመመስረት "Ethiopians had not internalized those (democratic) principles" ሲሉ ይህንን ሁሉ ተረድተው መሆን አለበት። እውቀት ምጥቀቱ እያለን ትክክለኛ መንገድ እንዳንመርጥ ያደረገንና የሚያደርገን ይኸው በንቃተ-ህሊናችንና በስነ-ልቡናችን ላይ የታተመ ማህተምና ድግምት ነው። በርግጥ ርግማን የሚባል ነገር አለ ከተባለ የእኛ ኢትዮጵያውያን ርግማን ይህ እንጂ ሌላ ነገር ሊሆን አይችልም። ተቃዋሚው መሃል ምሬትና ተስፋ መቁርጥ ገኖና ነግሶ የሚታየው ይህንን ማንነታችንን ስላልተረዳንና መቀይር ስላቃተን ነው። ገዥው ፓርቲም ቅራኔውችንና ተቃውሞዎችን ያጠፉና የገታ እየመሰለው ፍቱን የድምሰሳ መንገድ የሚመርጠውና ሁሉን አሳታፊ የፖለቲካ መድረክ እንዳይጠናከር እንቅፋት የሚሆነው በዝሁ የሁላችን የጋራ ማንነታችን ህመም ምክንያት ነው።

ከግዜ ርዝመት ጋር አጥንት ድረስ ዘልቆ የገባን የንቃተ-ህሊናና የስነ-ልቡና ልማድና ባህል ለመግራት እንዲህ በቀላሉ ባይቻልም ይህንን ችግር ሊገቱ ሊቀርፉና ሊያስወግዱ የሚችሉ ቅድመ-ሁኔታዎችን ማመቻቸትና መግንባት ግን ፍጹም የሚቻልና በአቅም ደረጃ የሚፈጸም ጉዳይ ነው። ከነዚህም ውስጥ፡-

አንደኛ) ትንሹና የመጀመሪያው ርምጃ ያለፈውን አስከፊ የታሪክ ምዕራፍ በአደባባይ መዝጋትና ከህሊናችን ማራቅ አስፈላጊ ይሆናል። ለዚህም ዋናው መሳርያ የግልና የጋራ ሱባኤን (soul search) ማበርታታትና የእርቅና የይቅርታን ባህል ማዳበር ነው። የይቅርታን ምንነትና ሃያል ዋጋ Reinhold Niebuhr እንዲህ ሲል ይነግረናል።“Nothing that is worth doing can be achieved in our lifetime; therefore, we must be saved by hope. ... Nothing we do, however virtuous, can be accomplished alone; therefore, we are saved by love. No virtuous act is quite as virtuous from the standpoint of our friend or foe as it is from our

standpoint. Therefore, we must be saved by the final form of love, which is forgiveness.”

ከዚሁ ጋር በማያያዝ በቅርቡ በሃይማኖት አባቶች የተጀመረው የደርግ አባላቱን ምህረት የማድረግ ርምጃም በዚሁ ጠቅላላ ሂደት ውስጥ መታየት የሚገባው ነው። የሃይማኖት አባቶቹ በተነሱበት በጎ ዓላማ እንዲገፉበትና በመንግስትም አስፍላጊውን ድጋፍ ይደርግላቸው ዘንድ በባህሉም በሃይማኖቱም በፍቅርና በእርቅ የሚያምነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ነው። ክርስቲያን ነን የምንል የክርስቶስን መንገድ አንቃወምም። መሃመድም የሚያስተምረን ይህንኑ ነው።

ሁለተኛ) ሁለተኛው መንገድ የፖለቲካ መድረኩን በተቻለ መጠን በአዲሱ ትውልድ መተካት ነው። ይህ የመተካካት የራሱ ተፈጥሯዊ ሂደቱን ተከትሎ እየተጓዘ ቢሆንም ተገቢውን እውቅናና ግፊት ሊሰጠው የሚገባ ነው። የብርትኳን ሚደቅሳ በፖለቲካ መድረኩ ላይ ጎልታ እንድትታይና በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ከምትወክለው ድርጅት ይልቅ ለሷ የነበረው አዎንታዊ አስተያየትና መልካም ግምት የመንጨው በሌላ ምክንያት ሳይሆን የአዲስ ሃይል፤ ቃፊርና ጀማሪ በመሆኗ ነው። በዋለልኝዝም የተበከለውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ አየር ለማጥራት አዳዲስ ትንፋሾችን ማብዛት ጠረኑን ለመለወጥ አስተዋጽዖው ትልቅ ነው።

ብርትኳን ራሷን ያገለለችው ለአጭር ግዜ ይሁን ለረዥም ባይታወቅም ምክንያቷን ግን መረዳትና መገመት አያዳግትም። ብርትኳን በቃሊቲ ቆይታዋ ያሰራት የኢህአደግ መንግስት ሳይሆን ከኢህአደግ በላይ ሌላ ትልቅ ሃይል እንዳለ ተረድታለች። ይህም ሃይል የኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክን የሚቆጣጠረውና ኢህአደግንም ተቃዋሚውንም ሁሉንም የሚያሽከረክረው ሃይል ዋለልኝዝም ይባላል። ብርትኳን ከዚህ ሃይል ጋር እንደተጋጨች አጢናዋለች። ብርትኳን ልክ ጨዋማና በተበከለ ባህር ውስጥ ገብታ የምትዋኝ የ fresh water አሳ አይነት ነበረች። ግን የባህሩ መርዛማነትና ጨዋማነት ንጹህ መንፈስዋና ያልተወሳሰበ ስብዕናዋ ሊቋቋመው አልቻለምና ንጹህ አየር ለመተንፈስ ከባህሩ ወጣች። ራሷን የማግለሏ ታሪክም በአጭሩ ይኸን አይነት ነው። ከመታሰሯ በፊት ፈተናዋ ምን እንደነበረ ዛሬ የሚያስታውሱ ጥቂቶች ናቸው።

ይህን ጉዳይ በሰፊ መነጽር ከተመለከትነው በርግጥም ይህንን ባህር ለማጽዳት ብርትኳንንና እንደ ብርትኳን የመሳሰሉትን አዲስ ንጹህ ትንፋሾች አዳዲስ ሰዎች በሁሉም ጎራና ድርጅቶች ማብቀሉና ማበርከቱ አስፈላጊነት በቂ ግንዛቤና ትኩረት የሚሻ ጉዳይ እየሆነ ከመጣ ሰንብቷል። በተቃዋሚው ላይ አሁንም አሁንም ራሱን ከሚደግመው የውድቀት ዙሪያ ቀለበት በጥሶ ለመውጣት ይህ አንዱ አይነተኛ አማራጭ መንገድ ነው። በኢህአደግም ውስጥ በነባር ታጋዮች ምትክ የኃ/ማሪያምና ደሳለኝና የመሳሰሉት መመረጥ ይህን የለውጥ አቅጣጫ ንፋስ ያሸተተና የተከተለ ይመስላል። ኃ/ማሪያም ደሳለኝን ከነባሮቹ የሚለየው አዲስ ትንፋሽ መሆኑ ነው። በዋለልኝዝም ሳይከተብ እንደ ስኮላር አገሩን እያገለገለ ለበለጠ ተሳትፎ ወደ ፖለቲካው የተቀላቀለ ነው።

ባለፉት ጊዜያት በዚህ የኢህአደግ ሹም ሽር ጉዳይ ላይ ብዙ አስተያየቶች ሲዘነዘሩ ቆይተዋል። ዋናው ቁምነገርና ሊሰመርበት የሚገባው ነጥብ የኃ/ማሪያም ስም ጓንጉል ወይም አንጌሳ ፤በሽር ወይም ተክለአብ መሆኑ ወይም አለመሆኑ ሳይሆን ለውጥ ሊያግዝ ይችላል ወይ የሚለው ጥያቄ ነው። አዳዲስ ሰዎችን ከሁሉም ጎራና ከሁሉም ድርጅቶች ወደ ከፍተኛ ሃላፊነት ማምጣት የጠቅላላ ፖለቲካ መድረኩን ባህልና ባህርይ የመቀየር እድል ሊያሰፉ ይችላል። እንደ ብርቱኳንና እንደ ኃ/ማሪያም አይነት አዲስ

ሰዎች ወደ ፖለቲካ መድርኩ መውጣት ትልቁ አስተዋጽዖ (እንደ ትምክህተኞቹ በዘር እንደ ዋለልኞቹ በመስዋዕትነት) የስልጣን entitlement ደዌ ያልተጠናወታቸው በመሆኑ ስልጣንን በድርጅት ውስጥ ከግለሰብ ወደ ግለሰብና በአገር ደረጃም ከድርጅት ወደ ድርጅት በሰላምና በርጋታ (smoothly) እንዲሸጋገር ስለሚረዱ ነው። ከዚህ እይታ አኳያ ይህ የስልጣን ሽግሽግ ለጠቅላላው የፖለቲካ ሂደት የኢህአደግ የበኩሉ አዎንታዊ መዋጮ ተደርጎ ሊቆጠርና ርምጃውም በአዎንታዊ ሊታይ ይገባዋል።

ሶስተኛ) ሶስተኛውና ለዲሞክራሲያዊ ስርአት መፈጠር ወሳኝ ሚና የሚጫወተው መንገድ የኢኮኖሚ እድገቱ ነው። ዲሞክራሲና ዲሞክራሲያዊ ስርአት መካካለኛ ገቢ ያለው ህብረተሰብ ክፍል ዘመናዊ የኑሮ ዘዴ ነው። የዚህ ህብረተሰብ ክፍል ባህል ነው። ያለዚህ ህብረተሰብ ክፍል ዲሞክራሲን ለመገንባት ማለም "ላም ባልዋለበት .." አይነትና ያለ መሰረትና ምሶሶ ጎጆ ለመቀለስ እንደመሞከር ይቆጠራል። የአገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ተረባርቦ ማፋጥን አገሪቱን ከድህነትና ከረሃብ ማላቅቅ ማለት ብቻ ሳይሆን የመካከለኛ ገቢ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል በማሳደግ ለዲሞክራሲ ማህበራዊ መሰረት መጣል ማለት ነው። መካከለኛ ገቢ ያለው ዘመናዊ የህብረተሰብ ክፍል በተጨባጭ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መስፍርቶች ላይ የተመሰረተ ተግባራዊ (pragmatic) ፖለቲካ የሚፈልግና የሚከተል በመሆኑ የአይዲዮሎጂና የጎጠኛ ፖለቲካ ስር አይሰዱም ይመክናሉ።

ከላይ እንደተዘረዘረው የእርቅና የይቅርታ መንገድ እንዲሁም የአዲስ ትውልድ ፖለቲከኞችን የመተካት ሂደት በአገራችን የፊውዳሊዝምንና የዋለልኝዝምን የፖለቲካ ባህል ቅርስና ውርስ ለማዳከምና ለመግታት የሚረዱ መንገዶች ሲሆኑ ሶስተኛው መንገድ የኢኮኖሚ እድገቱ መፋጠን ደግሞ የመጨረሻውን ምስማር በሳጥናቸው ላይ የሚመታ ወሳኙ መንገድ ይሆናል። የኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለዲሞክራሲያዊ ስርአት እውን መሆን ያለንን ምኞትና ተስፋ የሚያረጋግጥ ብቸኛ ዋስትና ነው።

በመሆኑም ነው በአሁኑ ጊዜ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ትኩረቱንና ጥረቱን ለእድገትና ለልማት በማድረግ በአንድ ልብ ተነስቶ ሲታይ ማየት ልብ የሚያሞቅ ተስፋ የሚፈንጥቅ ስሜት በሁሉም ዘንድ የሚፈጥረው። በአንድ ጥይት ሁለት ገድል ለመጣል ሁሉም ዲሞክራሲ ናፋቂና አገር ወዳድ ዜጋ ሁሉ ይህን ርብርቦሽ ማገዝና መርዳት ሊመካበት የሚገባው ተግባር ነው።

በአህጉራችን ትልቁን ዲሞክራሲና ጠንካራውን ኢኮኖሚ የገነባች አዲስ ሃያል (emerging power) ኢትዮጵያን በእድሜያችንና በአይናችን በብረቱ ለማየት ያበቃን። - አሜን።

ፍቅረ ህዝብ አሸናፊ

fekerehezb@live.com